የራስን ቢዝነስ ለመጀመር ሁለት አቅጣጫዎች

ለብዙ ዘመናት የሀገራችን ኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከመንግስት ጋር በመቆራኘቱ የተነሳ የግል ኢኮኖሚ ዘርፉ ብዙም አላደገም። ለዚህም ይሆናል አብዛኛው ሰው የራሱን ስራ ከመፍጠር ይልቅ በመንግስት ተቋማት ስራ ሲፈልግ የሚውለው። በስደት በምንኖርበት አገርም ትኩረታችን ወደግል ተቋማት ዞሮ እንደሆን እንጅ ያው ተቀጥሮ ለመስራት ያለን ፍላጎት አልተቀየረም። የዛሬው ፊቸር ጽሁፍ አላማም የራስን ቢዝነስ ለመጀመር እንዲቻል አቅጣጫ ማሳየት ነው።

የራስን ቢዝነስ ወይም ስራ ለመጀመር ሁለት አቅጣጫዎች አሉ።

የመጀመሪያውን ምርት ተኮር (Production Approach) እለዋለሁ። ግለሰቡ ራሱን የሚጠይቀው ጥያቄ "ምን መስራት እችላለሁ?" ብሎ ነው። ከፍላጎቱ ፤ ልምዱ፤ ስልጠናው ወዘተ በመነሳት ይህን መወሰን ይችላል። በዚህ ረገድ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ፍላጎቱን መከተሉ ላይ ነው።

በልጅነታችን ከትምህርት ቤት መልስ ሆነ ቅዳሜና እሁድ ስንሰራው የነበረ ነገር ካለ እንደጨዋታ የምንቆጥረው ነገር እንጂ እንደ ግዴታ የሚሰማን አልነበረም ፤ ያውም ክፍያ የማንጠይቅበት። ይህ ነው 'የልብ ፍላጎት' የሚባለው። ቢዝነስ ስንጀምርም ይህን ፈልገን ካገኘን ስራችን ሁሉ የጨዋታ ያህል የሚቀለን እና የሚያረካን ይሆናል። ስለዚህ ቢያንስ እስከሶስት ወር ጊዜ በመስጠት ከልጅነታችን ጀምሮ ምን ያስደስተን እንደነበር ማሰላሰል ይገባናል። ከተሳካልን ጥሩ ነው። ይህም ቢሆን ሌላ ጥያቄ ይቀረዋል። ይህውም ፤ ይህን ፍላጎት ወደ ቢዝነስ መቀየር ይቻላል ወይ የሚለው ነው። ቸዝ ሙጭ ውስ ፍላጎት ይላሙ ሶሙ ላዘህ ሙላሶ